የ2002 ዓመታዊ እቅድ

1.መግቢያ

በዞናችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለዉ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ከልማቱም ህዝቡን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ እንዲቻል መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ወሳኝ ነዉ፡፡ ስለሆም የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለዉጥ ትግበራን በአዳዲስ አሰራር ፣አደረጃጀትና በበቃ የሰዉ ሃብት ልማት አመራር በመታገዝ ፣በዘመናዊ ኢንፎርመሽን ቴክኖለጅ በማሳለጥና በማቀላጠፍ ተቋማዊ ለዉጥ እዉን ማድረግ ቁልፍ የትኩረት መስክ ሆኖ ተነድፏል፡፡ በዚህ መሰረት በየደረጃዉ የሚታዩትን የማስፈጸም አቅም ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ፈጥኖ ስልት በመቀየስ በተግባር ላይ እንዲዉል በማድረግና የሪፎርም ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል፡፡

በአጠቃላይ የ2002 በጀት ዓመት ዕቅድ በዋናነት የዲሞክራስና መልካም አስተዳደር ስርአት በማስፈን፡ በመንግስት ተቋማት ቀልጣፋና ዉጤታማ አሰራርን መዘርጋት መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የአቅም ግንባታ ሴክተር ባለፉት አመታት የከናወናቸዉን ተግባራትንና ያጋጠሙትን ችግሮች በመገምገም የተገኙ ዉጤቶች፣ አገራዊ የትኩረት አቅጣጫዎችንና የሰክተሩ ስትራቴጂያዊ ግቦች በዋና ግብአትነት በመዉሰድ የ2002 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደሚከተለዉ ተዘጋጅቷል፡

2. ያለፈዉ 2001 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም አጭር ግምገማ

*በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/ ጽንሰ ሀሳብ፤በለዉጥ አመራር ፣ በማስፈፀም አቅም ግንባታ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ወዘተ ላይ በዞን ሴክተር 19 መ/ቤቶች፣በ8ቱ ወረዳና 1ከተማ አስተዳደር ለ4306 አመራርና ሰራተኞች ፤ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ5572 ስልጠና በመስጠት ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡*ለውጡን በበላይነት ለመምራትና ለማስተባበር ቼክ ሊስት ተዘጋጅቶ ለ7ቱ ዞን ሴክቴር መ/ቤቶች፣ ለ8ቱ ወረዳዎችና ለ1ከተማ አስተዳደር ድጋፍና እገዛ በማድረግ በለውጡ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተለይተው ግብር መልስ ተሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ከተገባ በኂላ በተደረገው ግምገማ የሰው ኃይልና የቢሮ አደረጃጀት ምቹ ሆኖ በመደራጀቱ፣ተገልጋዮች ውጣ ወረድ ሳይበዛ አገልግሎት ከአንድ ቦታ ማግኘት በመቻላቸው፣ፈጻሚዎችም የሚሰጡትን አገልግሎት በኃላፊነትና በተጠያቅነት መንፈስ

ኃላፊዎችን ሳይጠብቁ ከጫፍ እስከ ጫፍ መወሰን በመጀመራቸው የተገልጋይ መጉላላት መቀነሱ እና የቲም መንፈስ በመፈጠሩ በተለይም በንግድ ኢንዱስትሪ፣በፋ/ኢ/ልማት እንዲሁም በፖሊስ ሴክተሮች አበረታች ውጤቶች ተመዝግቧል።

በ8ቱ መልካም አስተዳደር  መርሆች ላይ  ለ1958 አመራርና ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል።የአርብቶ አደር አካባቢ መልካም አስተዳደር ፓኬጅ ዝግጅቱ ተጠናቆ ረቂቁ ለአርብቶ አደር ወረዳዎች ተልኮ ግብረ-መልስ ተሰባስቦ ወደ ክልል ተልኳል። በወረዳና በዞን መልካም ተሞክሮን መቀመር ይቻል ዘንድ በዞን ደረጃ አብይ ኮሚቴና ቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ የመቀመሪያ ሰነዱ ለሁሉም ወረዳዎች ተልኮላቸዋል ኦረንቴሽንም ለወረዳዎች አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተሰጥቷል፤ በዚህም መሠረት ወረዳዎች መረጃዎችንን በማሰባሰብ የወረዳቸውን መልካም ተሞክሮ በመቀመር ላይ ናቸው። በዞን ደረጃ የሚቀመረው መልካም ተሞክሮ የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ በሁለት ቡድን ተከፍሎ በመስራት ላይ ይገኛል። በአርብቶ አደር ወረዳዎች በህግ ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ከአርብቶ አደር ወረዳዎች 7 ዕጩ ከአንድ ወረዳ በድምሩ 42 እና ከአርሶ አደር ወረዳዎች 4 ከእያንዳንዱ ወረዳ በአጠቃላይ 50 የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል።

የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በተቀናጀ ሁነታ ተግባራዊ ለማድረግ  በታቀደዉ መሰረት በ15 ቀበሌያት ለሚገኙ ለ75 ማህበራዊ ፍርድቤት ዳኞች  በፍትህ አሰጣጥ  ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል። የፍትህ ስርዓት ማሻሻያን በተመለከተ በሁሉም ከተማና ገጠር ቀበሌዎች የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር ድጋፍና ክትትል ተደርጓል። የፍ/ቤቶች ተደራሽነትና ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት  ተዘዋዋሪ ችሎት በ4 ወረዳዎች በተጠናከረ መልኩ እየተዳሄደ ይገኛል።እንዲሁም የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በበላይነት ለማስተባበር የፍትህ ሥርዓት ማሻሸያ ፕሮጀክት ተዘጋጅቶ ከፍትህ መ/ቤቶች ጋር ተፈራርመን  ወደ ሥራ በመግባት ድጋፍና እገዛ እየተደረገ ነው።

የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ክፍተት ዳሰሳ ጥናት ለማድረግ በታቀደዉ መሰረት በ375 በዞን፣ በወረዳና በጂንካ ከተማ ባሉት የሥራ ሂደቶች ላይ የሚያስፈልግ የሰዉ ኃይል 1363 ፣ የተመደበ 438(32.13)፣ ክፍት መደብ 925(67.7) ሲሆን ከክፍት መደቦች የመጀመሪያ ድግርና  በላይ የሚጠየቀዉ 187(20.22) ድግር ወይም  ዲፕሎማ የትምህርት ደረጃ የሚጠይቅ መደቦች 738(79.78) ይሆናሉ::  እስከ75% የሰዉ ሀይል ያልተሟላባቸዉ 274 የሥራ ሂዶቶች  582

የሰዉ ሀይልና ለአንድ ወር ደመዎዝ የበጀት መጠን ብር 695114.00 የሚያስፈልግ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የሲቪል ሰርቪሱን የተማረ ሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ  በተያዘው ዕቅድ 95 በመጀመሪያ ዲግሪ  በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በመደበኛና በርቀት ትምህርት ለመማር የተፈተኑና ስማቸው የተላለፉት ዉጤታቸዉን እየተጠባበቁ ይገኛሉ፡፡

I.C.T:-የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ በዞን ደረጃ የICT ስትሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡የኮምፒውተር ስልጠና ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሠረት በዞን ማዕከል 100 ሲቪል  ሰርቫንቶች ስልጠና አግኝቷል፡፡       ቀበሌያትን የዘመናዊ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ተጠቃሚ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት 64 ቀበሌያት በየሽቦ አልባ ስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የሐመር ወረዳ በሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም. 5 ኮምፒውተሮች ከክልል አቅም ግንባታ ድጋፍ በመገኘቱ የመረጃ ማዕከል ተቋቁሞ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡በዞን መረጃ ማዕከል ውስጥ 220 ሰዎች በተደጋጋሚ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡  የጥገናና የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ ውስጥ የተለያዩ ሶፍት ዌሮች ለወረዳዎች ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ በዞንና ወረዳዎች 22 ኮምፒውተሮች ጥገና በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ከብር16800.00 ያላነሰ የመንግስት ወጪ ድኗል፡፡ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ለተገበሩ የሥራ ሂደቶችን ኮፒውቲራዝ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት 10 ኮምፒውተር እና 30 እስካነሮች በዞን በ8 ወረዳዎችና አንድ ከተማ አስተዳደር ተሰራጭቷል፡፡

በምልመላና መረጣ መመሪያ ላይ ኢንስፔክሽንና ድጋፍ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት በወረዳዎች ላይ በ10 ጽ/ቤቶች የኢንስፔክሽን፣ በ3 ጽ/ቤቶች ላይ ድጋፍና ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የ2000 ዓ.ም. የ40 መ/ቤቶች መረጃ ተሰባስቦ ተደራጅቷል፡፡ በሰሜን አሪ ወረዳ በ4 መ/ቤቶች ላይ አለአግባብ ተከፍሎ የባከነ 19,112.00 / አስራ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ አስራ ሁለት ብር/ ተመላሽ ተደርጓል፡፡ከተለያዩ መ/ቤቶች ሃያ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ቀርበው በቂ ምላሽ አግኝተዋል

4. ዓለማ

የመንግስት ተቋማትን አቅም የማስፈጸም አቅም በመገንባት ፈጣንና ቀጣነት ያለው ልማት በማረጋገጥ በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት ነው፡፡

5. የሴክተሩ ቁልፍ፣አበይትና ንዑሳን የትኩረት መስኮች

5.1 ቁልፍ የትኩረት መስክ

የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራን በአዳዲስ አሠራር፣አደረጃጀትና በበቃ ሰው ሃብት ልማትና አመራር በመታገዝ፤በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማሳለትና በማቀላጠፍ ተቋማዊ ለወቅጥ/Organizationnal Transformation/ እውን ማድረግና መልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት

5.2 አበይት የትኩረት መስኮች፡-

- በሆኑ መንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት፣ሪፖርቴ አቀራረብ ሥርዓትና የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት
- በሴክተሩ የሚከናወኑት ተግባራትን በመጽሔት፣በበራር ጽሑፎችና በልዩ ልዩ የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች በማጀብ ለህዝብ ወቅታዊ መረጃ እንዲደርስ ማድረግ
- የሴክተሩ አመራር  በሥርዓት ጾታና በፀረ-ኤች አይ ቪ ኤድስ እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራና የመሪነት ሚና  እንዲጫወት ማድረግ
- ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ክፍተቶችን ለመሙላት የተደረጉ ጥረቶች

6. የአቅም ግንባታ ሴክተር ግቦች

6.1 በቁልፍ የትኩረት መስክ

ግቦች

1. የመሠረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ዳይመንዱን የተሟላ ለማድረግ ከክልል ተጠንተው በሚወርዱ የጥናት ውቴቶች ሥራ ላይ ማዋል
2. በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በተሟላ ሁኔታ የተተገበረ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/
3. በሁሉም መንግስት ተቋማት የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ/BSC/አሠራር
4. በሁሉም መንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሠራር

5. በዞኑ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋና በተጠናከረ ሁኔታ ሥራ ላይ የዋለ አንድ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሠራር
6. በሁሉም የዞኑ ቀበሌያት መዋቀር አሳምኖ ማሠራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን በማስፋፋት ረገድ የተደረገ ድጋፍ
7. በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሠራ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ
8. በሁሉም አርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ ተደረጎ የተተገበረ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ
9. በሁሉም ቀበሌያት የኮሚዩኒቲ ፖሉስንግ ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ የተደረገ ድጋፍና ክትትል
10.በሁሉም የፍትህ ተቋማት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበር ተደራሽ፣ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል
11.በመልካም አስተዳደርና በሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራሞች የአፈጻጸም ስኬቶች  እና ጉድለቶች ላይ የተደረገ አንድ የፋይዳ ጥናት
12.በምንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም የመንግስትና የግሉን ሴክተር ለማጠናከር አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል
13.በዞኑ የተዘረጋና የተስፋፋ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት/ማህበረሰብ መረጃ ማዕከል፣ወረዳ ኔት፣እስኩል ኔት፣WAN,LAN,,,/
14.የአስቀጣይ ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ለማሰደግ የተፈጠረ አቅም
15.100% በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ
16. 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈጻጸም ችግሮች፣ቅሬታዎችና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች
17.በስልጠና አቅሙ የተጎለበተ የዞን፣የወረዳና ከተማ 144176 አስተዳደር አመራርና በለሙያ እንዲሁም ለመንግስት ሠራተኞች በመንግስት ፖሊስና  በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ፅንሰ ሃሳብ ላይ የተሰጠ ስልጠና የምክር አገልግሎት
18.ግብርናና ገጠር ልማት  እና ሥራና ከተማ ልማት ተቋማትን እመርታዊ ለውጥ እንዲመጡ ከማድረግ አንጻር የተደረገ የአቅም ግንባታ ድጋፍ
19.ቢሮውን አሠራር ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የተገነባ አንድ የኢንፎርሜሽን ኮምንኬሽን ሕንጻ፣የንብረት መካዝን፣የግቢ ሣይት ወርክ የተገዙ 3 ፒካፒ መኪናዎችና ለአደራሽ ለክክል፡፡

6..2 አበይት የትኩረት መስኮች

ግቦች

1. በዞኑ የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተቀናጀ የዕቅድ አዘገጃጀት፣ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓትና የተዘጋጀ የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ
2. በሴክተሩ የተፈጠረና በተጠናከረ መንገድ የተተገበረ አንድ የሥርዓተ ፆታና ፀረ-ኤች አይ ቪ ኤድስ ስትራቴጂ
3. በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ለህብረተሰቡና ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ የሴክተሩ ወቅታዊ መረጃዎች
4. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ክፍተቶችን ለመሙላት የተደረጉ አንድ ጥናት

7. የሴክተሩ ግቦችና የሚጤበቁ ውጤቶች

7.1 በቁልፍ የትኩረት መስክ

1. የመሠረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ዳይመንዱን የተሟላ ለማድረግ ከክልል ተጠንተው በሚወርዱ የጥናት ውጤቶች ሥራ ላይ ማዋል
    - ከBPR ጋር የተጣጣመ የሥራ ምዘናና ደረጃ አሰጣጥ ሥርዓት
    - በውጤት ተኮር ላይ የተመሠረተ የማትጊያ ክፍያ ሥርዓት
    - የማወዳደሪ ዕውቅናና ማበረታቻ ሥርዓት/Charter and Charter mark/
    - ከኃላፊነት የሚነሱ ተሻሚዎች ጥቅማ ጥቅም ለማስጠበቅ የተዘረጋ ሥርዓት
    - የከፍተኛ አመራር ሥርዓት/senior executives service/
2. በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በተሟላ ሁኔታ የተተገበረ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/
    - የሁለተኛ ዙር BPR ለሚተገበሩ 4615 ሴክተር መ/ቤት ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ለሙሉ ትግበራ የተሰጠ ስልጠና
    - በሁሉም መንግስት ተቋም የመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ ለመተግበር የተደረገ ድጋፍና ክትትል
3. በሁሉም መንግስት ተቋማት የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ/BSC/አሠራር
    - የተሰራጨ አንድ የውጤት ተኮር ማስፈጸሚያ ማኑዋል
    - በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች አራት ጊዜ የተደረገ የውጤት ተኮር ዕቅድ/BSC/ አተገባበር ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ

- ❖ በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ አንድ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሠራር
- ❖ በዞኑ በበሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋና በተጠናከረ ሁኔታ ሥራ ላይ የዋለ አንድ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሠራር የተደራጀ አንድ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አሠራር

4. በሁሉም መንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሠራር
   - ❖ የተገልጋዮች ቅሬታ ለመፍታት የተዘጋጀና የተተገበረ አንድ የተቋም ቻርተር
5. በዞኑ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋና በተጠናከረ ሁኔታ ሥራ ላይ የዋለ አንድ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሠራር
   - ❖ አንድ የተዘጋጀ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን መመሪያ
   - ❖ አንድ የተዘጋጀ የኢንፔክሽንና ሱርቪዥን አሠራር ስልጠና ሰነድ
   - ❖ ለሁሉም ወረዳና ቀበሌያት ለ254 አመራሮች የኢንስፔሽን ቡድን አባላት በኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን ማስፈጸሚያ መመሪያና በኢንስፔክሽን አሠራር ወደ ሥራ ለማስገባት የተሰጠ ስልጠና
   - ❖ በሁሉም ቀበሌት በፓኬጁ መሠረት የተቋቋመና ሥራ የጀመረ የኢንስፔክሽን ቡድን
   - ❖ አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፍ፣ግብረ መልስና ሪፖርት
6. በሁሉም የዞኑ ቀበሌያት መዋቀር አሳምኖ ማሠራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን በማስፋፋት ረገድ የተደረገ ድጋፍ
   - ❖ 50% ሞደል ግለሰቦች መንደሮችና ቀበሌያት እንዲመረጡ የተደረገ የቴክኒክ ድጋፍ
   - ❖ የቀበሌ ምክር ቤት፣ የብዙሃን ማህበራት እንዲሁም የባህላዊ ተቋማት ተሳትፎን ለማጎልበት አራት ጊዜ የተሰጠ ምክርና ድጋፍ
   - ❖ በዞን ደረጃ የተጠናከረ አንድ የምርጥ ተሞክሮ ሰነድ
7. በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሠራ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ
   - ❖ የተጠናከረ በየቀበሌያት ደረጃ የተዘረጋው የቅሬታ ማስተናገጃ፣የመረጃና የጉዳይ አቀባበል አሠራር ሥርዓት
   - ❖ የገጠር ልማት ተግባሮች በቀበሌ ደረጃ ተጣምሮና ተቀናጅቶ ወደ ተግባር የሚወርድበት የዕቅድ አዘገጃጀትና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት

- ❖ አራት የልማት ኮሚቴዎች በተቀናጀ ሁኔታ የሚሰሩበትን አሠራር በተጠናከረ መንገድ ማስቀጠል

8. በሁሉም አርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ ተደረጎ የተተገበረ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ
   - ❖ ተመልምለው የሰለጠኑ የሁሉም ቀበሌ ሥራ አስኪያጆች
   - ❖ በፓኬጁ መሠረት ሁሉም የቀበሌ አመራሮች የተሰጠ ስልጠና
   - ❖ በፓኬጁ ላይ ለ5000 ፈጻሚ ሠራተኞችና ለአርብቶ አደሩ ህብረተሰቡ የተሰጠ ስልጠና
   - ❖ ለአርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስረተዳደር ፓኬጅ ማስፈጸሚያ የተዘጋጁ 2 መመሪያዎች
   - ❖ የመልካም አስተዳደሩ ፓኬጅ በአከባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን የተሰጠ ድጋፍና ክትትል
9. በሁሉም ቀበሌያት የኮሚዩኒቲ ፖሎስንግ ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ የተደረገ ድጋፍና ክትትል
   - ❖ በሁሉም በዞኑ ከተማና ገጠር ቀበሌዎች የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ እንዲጠናከር የተዘረጋና ሥራ ላይ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል
10. በሁሉም የፍትህ ተቋማት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበር ተደራሽ፣ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል
    - ❖ ከአርብቶ አደር አከባቢ ተመልምለው የህግ ትምህርት ለሚያጠኑ 50 ዲፕሎማ ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ
    - ❖ አጫጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና ለሚወስዱ የህግ ባለሙያዎችና ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍዊ ክትትል
    - ❖ በዞኑ የፍትህ ተቋም አሠራራቸውን ለማሻሻል የተደረገ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ድጋፍ
    - ❖ እጅ ከፍንጅ ለተያዙ ወንጀለኞች የዕለት ፍርድ ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፍና ክትትል
    - ❖ የፍ./ቤቶችን ተደራሽ/E-litigation/ ቀጣይነት ባለው መልክ ለማስፋፋት አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፍዊ ክትትል
11. በመልካም አስተዳደርና በሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራሞች የአፈጻጸም ስኬቶች  እና ጉድለቶች ላይ የተደረገ አንድ የፋይዳ ጥናት

- ❖ በመልካም አስተዳደርና በሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራሞች አፈጻጸም ስኬትና ጉድለት የያዘ  አንድ የጥናት ሰነድ

12.በምንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም የመንግስትና የግሉን ሴክተር ለማጠናከር አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል

- ❖ በቴ/ሙ/ት/ሥ/ የለውጥ ሥራዎች ላይ የተሰጠ አራት ጊዜ ክትትልና ድጋፍ
- ❖ ለደረጃ አንድ ሁለት የሙያ መስክ የተዘጋጀ ሙያዊ ደረጃ መስፈርት ላይ አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፍና ክትትል
- ❖ ተቋማት በቅንጅት የእሴት ሰንሰለት እንዲመርጡና እንዲተገበሩ አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፍ

13.በዞኑ የተዘረጋና የተስፋፋ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት/ማህበረሰብ መረጃ ማዕከል፣ወረዳ ኔት፣እስኩል ኔት፣WAN,LAN,,,/

- ❖ ለዞንና ለወረዳና ለከተማ ሴክተር መ/ቤቶች ተገዝተው ተሰራጭ 50 ኮሚፒውተሮችና ተጓዳኝ ዕቃዎችና እንዲሁም የተጠኑ  ኮሚፒውቴሮች
- ❖ በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ለሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች በመሠረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም አድቫንስድ የኮምፒውቴር ክህሎት ስልጠና
- ❖ ለሴክተር መ/ቤቶች 4 ጊዜ የተደረገ ድጋፍና ክትትል

14.የአስቀጣይ ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ለማሰደግ የተፈጠረ አቅም

- ❖ የICT ቁሳቁስ /10 ላፕቶፕ/ እንድሟላ የተደረገ ድጋፍ
- ❖ ለሰው ሃብት አመራር የሥራ ሂደት 1000 ፈጻሚዎች በJEG,BSC,PRP  ዙሪያ የተሰጠ ስልጠና

15. 100% በዘመናዊ የመረጃ  አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞችአጠቃላይ

- ❖ ወቅቱን ጠብቀው እና በአግባቡ ተደራጅተው የተቀመጡ የሰው ሃይል መረጃ
- ❖ ለተገልጋዮች የተሰጡ መረጃዎች

16. 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ችግሮች ቅሬታዎችና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች

- ❖ለቀረበ ቅሬታ ተጣርቶ የተሰጠ ውሳኔ
- ❖ ለቀረበ ቅሬታ በስፍራው በአካል ተገኝቶ የተጣራና የተሰጠ ውሳኔ
- ❖ የተፈፀመ የቅሬታ ውሳኔ

- ❖ በሰው ሀብት አመራር የአፈፃጸም ክፍተት መነሻ ለቀረበ የይግባኝ ጉዳይ ውሳኔ መስጠት
- ❖ በመደበኛ ስሚ ሂደት ተጣርቶ የተሰጠ ውሳኔ
- ❖ በአካል ተገኝቶ ማስረጃ ማጣራትና በተዘዋዋሪ ችሎት የተሰጠ የይግባኝ ውሳኔ

17. በስልጠና አቅሙ የጎለበተ የዞን የወረዳና የከተማ 144176 አስተዳደር አመራርና ባለሙያ እንዲሁም ለመንግስት ሠራተኞች በመንግስት ፖሊሲና በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ፅንሰ ሃሳብ ላይ የተሰጠ ስልጠና የምክር አገልግሎት

- ❖ የለውጥ አመራር ሥልጠና ያገኙ የወረዳ 1690 አመራር አካላትና ባለሙያ
- ❖ በBSC ለ 526 አመራር የተሰጠ ስልጠና
- ❖ ምደባ ያላገኙና ተመልምለው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የገቡ 20 ሠራተኞች
- ❖ በሰ/ሀ/ልማት ስትራቴጂ መመሪያ ላይ ሥልጠና የተሰጣቸው 20 ፈሚዎች
  ለአራት ሴክተሮች/የተገልጋዮችን/ ፍላጎት መሠረት አድርጎ የተሰጣቸው 392 ፈፃሚዎች
- ❖ ለሰው ሀብት ልማት ፡ለላውጥ ፕሮግራሞች አስተባባሪዎችና ለሰው ሀብት ሥራ አመራር 9 ባለሙያዎች በመሰረታዊ የአመራር ክህሎት ላይ የተሰጠ ሥልጠና
- ❖ የአገር ውስጥና የውጪ ሀገር የትምህርት ዕድሎችን ለ50 ሰልጣኞች በማፈላለግ የተከናወነ የማስተባበር ሥራ
- ❖ የተሰጡ ሥልጠናዎች በትክክል ስለመተግበራቸው 2 ጊዜ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ
- ❖ ለ 30 ለሰ/ሀ/ልማትና ለለውጥ ፕሮግራም ባለሙያዎች የተሠጠ የአሰልጣኞች ሥልጠና
- ❖ ለ254 የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች በመንግስት ፖሊሲዎች ፤ፕሮግራሞች በአመራርና በቀበሌ ሥራአስኪያጆች ተግባርና ሐላፊነት ላይ የተሰጠ ሥልጠና
- ❖ ለ5000 የመንግስት ሠራተኞች በመንግስት ፖሊሲዎች ፕሮግራሞችና በመልካም አስተዳደር ፡ BPR እንዲሁም በለውጥ ፕሮግራሞች የተሠጠ ሥልጠና
- ❖ ለ190 መ/ቤቶች የአፈፃፀም መመሪያዎችና መስፈርቶች ማዘጋጀት ፤ ማስተዋወቅና ማሰራጨት

- ❖ በተዘጋጁ በአዳዲስና ነባር 8 መመሪያዎች  ላይ ለ5000 የተሰጠ ስልጠናና ምክር

18 . ግብርናና ገጠር ልማት እና ሥራና ከተማ ልማት ተቋማት እምርታዊ ለውጥ

እንዲያመጡ ከማድረግ አንፃር የተደረገ የአቅም ግንባታ ድጋፍ

- ❖ በጥቃቅን አነስተኛ ተቋማት ለተደራጁና በሥራ ላይ ላሉ ሰዎች የተሰጠ ደጋፍ
- ❖ በአግሮፕሮሰሲንግ፦ በቆዳ እና በቀርከሀ አመራረት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እንዲሰጥ የተደረገ ድጋፍ
- ❖ ተቋማት በቅንጅት የእሴት ሠንሰለት እንዲተገብሩ የተደረገ ድጋፍ፤
- ❖ በዞኑ በከተማና በወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች የኔት ዎርክ ዝርጋታ ማከናወን
- ❖ የጥርብ ድንጋይ ንጣፍሥራ ባጀትሥራ እንዲጀምሩ ድጋፍ የተደረገላችው የሪፎርም ከተሞች፤
- ❖ በዞን፣በወረዳና በከተሞችአገልግሎት አሰጣጡን ሊያቀላጥፉ የሚችሉ የሶፍት ዌርናየድረገፅ ሥራዎችን መስራትና ማሰራት በተለይም በከተማ ማዘጋጃ ቤት ያለውን የመረጃ አያያዝና አሰራር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አእንዲሆ ንማስቻል
- ❖ በሪፎርም ከተሞች ያለውን የግብር አሰባሰብ ሥራ ሊያቀላጥፍ የሚችል ስርዓት መዘርጋት
- ❖ አርሶአደሩ የገበያ መረጃና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስረዓት መፍጠር
- ❖ በገጠርና በከተማ የሚገኙ የማህበረሰቦች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል
- ❖ የማህበረሰብ መረጃ ማዕከሎችን ማቋቋም
- ❖ በመንግስት ለተቋቋሙት የማህበረሰብ መረጃ ማዕከሎችን የአሰራር መመሪያ ማውጣት

19. ቢሮውን አሰራር ቀልጣፋና ውቴታማ ለማድረግ የተገነባ አንድ የኢንፎርሜሽን ኮምኒኬሽ ሕንጻ የንብረት መጋዘን ፣የግቢ ሳይትወርክ የተገዙ 3 ፒካፕ መኪናዎችና አንድ ዳታ ሴንተር ለማደራጀት አዳራሽ ዕድሳትና  ለክፍፍል፡፡

- ❖ አንድ የተገነባ የንብረት መጋዘን
- ❖ አንድ የተገነባ የኢንፎርሜሽን ኮምኒኬሽን ቴክኖሎጂ

- ❖ አዳራሽ እድሳትና የመከፋፈል ሥራ
- ❖ የተሰራ የግቢ ሳይትዎርክ

7.2/ በአበይት የትኩረትመስኮች

20. በክልሉ የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሠራ ለይ የዋለ የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት

ሪፖርት አቀራረብ ስርዓትና የተዘጋጀ የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ

- ❖ የተዘጋጀ የቀጣይዓመትና የ5 አመት የተቋም ስትራቴጂ ዕቅድ
- ❖ በሁሉም የመንግስት ተቋማትና በየደረጃው ባለው እርከን የተዘረጋ የዕቅድ የሪፖርት አቀራረብና የግኑኝነት ሥርዓት

21. በሴክተሩ የተፈጠረና በተጠናከረ መንገድ የተተገበረ የሥርዐተ ፆታና ኤች

አይ ቪ ኤድስ

- ❖ የሴክተሩን ሠራተኞችየሥርዓተፆታና ፀረ-ኤች አይ ቪ ኤድስ ለመግታት የተሰጠ ሥልጠና
- ❖ ኤች አይ ቪ ኤድስን በሴክተሩ ሰራተኞች ለመከላከል ለዞንና ለወረዳ ለመግታት የተደረገ ድጋፍና ክትትል
- ❖ የስርዓተፆታና ፀረ-ኤች አይ ቪ ኤድስ በየወሩ 12 ጊዜ የተደረገ ውይይት

22. በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ለህብረተሰቡና ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ የሴክተሩ

ወቅታዊ መረጃዎች

የተዘጋጀ በራሪ ፓምፕሌት ፣መጽሔት፣ቪድዮናዶክመንተሪ ፊልም

- ❖ በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ በቴሌቪዥንና በሬድዮ ለህዝብ የተላለፈ መረጃ
- ❖ የሥርዓተ ፆታ ምንነትና ኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያየተዘ

23.ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ክፍተቶች ለመሙላት የተደረጉ ጥናቶች

- ❖ የተዘጋጀ የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂ
- ❖ የተዘጋጀ የዞኑ የሰ/ሀ/ልማት ስትራቴጂ የአፈጻጸም መመሪያ
- ❖ የተካሄደ የስልጠና ፍላጎት ጥናት
- ❖ በተለያዩ የሥልጠና ርእሶች ላይ ደረጃቸውን ጠብቀው የተዘጋጁ ሞጁሎች
- ❖ የተሻሻለ የአገር ውስጥና የውጭ አገር የትምህርት ዕድል የአፈጻጸም መመሪያ

❖ በአቅም ግንባታ ፕሮግራም የሥረዓተ ፆታ ላይ የጠካሄደ የዳሰሳ ጥናት የተገልጋዮች እርካታ ደረጃ